# የተሻሻለው የሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ-መንግስት

## አዋጅ ቁጥር ፵፯/፲፱፻፺፭ ዓ/ም

መስከረም ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ/ም

ሐረር

Scanned by CamScanner

# አዋጅ ቁጥር 46/1997 ዓም

# የሐረሪ ህዝብ ክልል ህገ-መንግስት ማሻሻያ አዋጅ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ ‹‹ የሐረሪ ህዝብ ክልል የተሻሻለው ህገ-መንግስት ማጽደቂያ አዋጅ›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ህገ-መንግስቱን ስለማሻሻል**

ጳጉሜ 6 ቀን 1987 የጸደቀው የክልሉ ህገ-መንግስት ድንጋጌዎች ይዘትና አቀማመጥ ከታየ በኋላ የሐረሪ ህዝብ ክልል የተሻሻለው ህገ-መንግስት በዚህ አዋጅ ጸድቋል፡፡

3. **ስለ ነባር ህጎች ተፈጻሚነት**

በስራ ላይ ያሉ ህጎች ከተሻሻለው ህገ- መንግስት ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

4. **ህገ- መንግስቱ በስራ ላይ ስለሚውልበት ጊዜ**

የሐረሪ ህዝብ ክልል የተሻሻለው ህገ- መንግስት ከመስከረም 30/1997 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ሐረር መስከረም 30 ቀን 1997 ዓ/ም**

**ፉአድ ኢብራሂም**

**የሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት ፕሬዝዳንት**



Scanned by CamScanner

# መግቢያ

እኛ የሐረሪ ህዝብ ክልል ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሲደርስባቸው የነበረውን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊና ኃይማኖታዊ ጭቆና፣ ጫናና ተጽእኖ በተለያየ ስልት ፣መልክና ቦታ ሲታገሉ ቆይተው በመጨረሻ በግንቦት ወር 1983 ዓ/ም ለዚሁ ሁሉ ምክንያት የሆነውን ስርአት በማያዳግም ሁኔታ ለመጣል በመቻሉ በተለይ ጭቁን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር፣ ታሪካቸው፣ ባህላቸውና ቋንቋቸውን ለማዳበር ባጠቃላይ ብሔራዊ ህልውናቸውን ለመጠበቅ የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታ መፈጠሩንና ይህም ህዳር 29 ቀን 1987 ዓ/ም በኢትዮጵያ ህዝቦች በጸደቀው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት መረጋገጡን በመገንዘብ፣

የሐረሪ ህዝብ ምንም እንኳ በምዕተ-አመታት ለሚቆጠር ዘመን ራሱን በራሱ ያስተዳድር፣በራሱ ታሪክ ወግና ባህል ይኮራ የነበረ ቢሆንም በ1886 ዓ/ም በተደረገበት ወረራ በነፍጠኛው ስርአት ስር ከመውደቁም በላይ ይህንን ስርአት ለማስወገድ በተለያዩ ጊዜያት ባደረገው ንቅናቄና ትግል ምክንያት ለግርፋት፣ ለእስራትና ብሎም ለስደት በመዳረጉ በራሱ ክልል በቁጥር አናሳ መሆኑ የተነሳ ልዩ አወካከል ስልት ማስፈለጉን በመረዳት፣

የሐረሪ ህዝብ ሲደርስበት የነበረውን ግፍና ጭቆና ሲካፈሉ ከነበሩት ከአካባቢው የኦሮሞ ህዝብ እና ከሌሎች የክልሉ ነዋሪ ህዝቦች ጋር በመሆን የክልሉን አስተዳደር በጋራ ማቋቋምና መምራት ያለባቸው መሆኑን በማጤን፣

በክልላችን ውስጥ ዘላቂ ሰላምና ዋስትና ያለው ዲሞክራሲ እንዲሰፍን



Scanned by CamScanner

የግለሰብና የብሔር ብሄረሰብ መሰረታዊ መብቶች የተከበሩበትና ከታሪካችን የወረስነውን የተዛባ አመለካከትና ግንኙነት በማረምና በማስተካከል መልካም አስተዳደርና የህግ የበላይነት የሰፈነበት ስርዓት መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በተለይም እኛ የሐረሪ፣የኦሮሞና ሌሎች ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የተፋጠነ የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት ፍትኃዊ የስልጣን ክፍፍል እንዲኖር በተለይም ሦስቱን የመንግስት አካላት የስልጣን ክፍፍልና በመካከላቸው የሚኖረውን ግንኙነት በግልጽ ማስቀመጥና ተጠያቂነታቸውንም በግልጽ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በዚሁ መሰረት እኛ የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት አባላት የመረጠንን ህዝብ በመወከል ከዚህ በፊት ተመክሮበት የጸደቀውንና በስራ ላይ ያለውን የክልሉን ህገ-መንግሥት በጥልቀት ተመልክተን ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በተገናዘበ መልኩ ተሻሽሎ የቀረበውን ህገ-መንግሥት መክረንበትና ተወያይተንበት ዛሬ መስከረም 30 ቀን 1997 ዓ/ም በሙሉ ድምፅ አጽድቀነዋል።



Scanned by CamScanner

## ምእራፍ 1

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1
### የክልሉ መንግስት ስያሜ

የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ተብሎ የሚጠራ ዲሞክራሲያዊ መዋቅር ያለው መንግስት በዚህ ህገ-መንግስት ተመስርቷል።

### አንቀጽ 2
### የሐረሪ ህዝብ ክልል ግዛት ወሰን

የሐረሪ ህዝብ ክልል በሰሜን በኮምቦልቻና በጃርሶ ወረዳዎች፣ በምስራቅ በጉርሱምና በባቢሌ ወረዳዎች፣ በደቡብ በፌዲስ ወረዳና በምእራብ በአለማያ ወረዳ የሚዋሰን ነው።

### አንቀጽ 3
### ሰንደቅ አላማና አርማ

1. የሐረሪ ህዝብ ክልል ሰንደቅ አላማና አርማ ይኖረዋል። ሰንደቅ አላማውም መደቡ ነጭ ሆኖ ከላይኛው ጠርዝ ገባ ብሎ ወደ አግድም የሚዘልቅ ቀይ መስመር ሲኖረው ከታችኛው ጠርዝ ከፍ ብሎ ወደ አግድም የሚዘልቅ አረንጎዴ መስመር ይኖረዋል። በቀዩና በአረንጓዴው መስመር መካከል ዓርማ ይኖረዋል።
2. የሰንደቅ አላማው ቀለማት የሚያስተላልፉት መልእክት፣
   ሀ. ነጩ መደብ የክልሉ ህዝብ በፍትህና በእኩልነት ላይ ለተመሰረተ ሰላም ያለውን ስሜትና ፍላጎት ያመለክታል፣
   ለ. ቀዩ መስመር ህዝቡ ለመብቱና ለነፃነቱ ያደረገውን ትግልና የከፈለውን መስዋእትነት ያመለክታል፣
   ሐ. አረንጎዴው መስመር ህዝቡ ለልማትና ለእድገት ቆርጦ መነሳቱንና የወደፊቱን ብሩህ ተስፋ ያመለክታል።



Scanned by CamScanner

## አንቀጽ 4
## የክልሉ መዝሙር

የሐረሪ ክልል ህዝብ የረጅም ዘመን የጀግንነትና የፍትህ ታሪክ እንዲሁም የተገኘውን ድል የሚያሳይና ለተሻለ ኑሮ ያለውን ምኞት የሚያንፀባርቅ የራሱ መዝሙር ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 5
## ርዕሰ ከተማ

የሐረሪ ህዝብ ክልል ርእሰ ከተማ ሐረር ነው፡፡

## አንቀጽ 6
## የስራ ቋንቋ

የሐረሪ ህዝብ ክልል የስራ ቋንቋ ሐረሪ እና ኦሮምኛ ናቸው፡፡

## አንቀጽ 7
## የፆታ አገላለጽ

በዚህ ህገ- መንግስት ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

# ምእራፍ ሁለት
# የህገ- መንግስቱ መሰረታዊ መርሆዎች

## አንቀጽ 8
## የህዝቡ የስልጣን ባለቤትነት

የሐረሪ ህዝብ የክልሉ የበላይ ስልጣን ባለቤት ሲሆን፣ የሕዝቡ የበላይነትም የሚገለጸው በዚህ ህገ-መንግስት መሰረት በሚመርጣቸው ተወካዮችና ራሱ በሚያደርገው ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነው፡፡

## አንቀጽ 9
## የሕገ- መንግስት የበላይነት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት የበላይነት



Scanned by CamScanner

እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. ይህ ህገ-መንግስት የክልሉ የበላይ ህግ ነው፡፡ ማንኛውም ህግ፣ ልማዳዊ አሰራር ወይም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከዚህ ህገ-መንግስት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡
2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ፣ የመንግስት አካል፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስልጣኖቻቸው ይህን ህገ-መንግስት የማክበርና ለህገ መንግስቱ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው፡፡
3. በዚህ ህገ-መንግስት ከተደነገገው ውጪ በማናቸውም አኳኋን የመንግስት ስልጣን መያዝ የተከለከለ ነው፡፡

## አንቀጽ 10
## ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች

1. ሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው፡፡
2. በክልሉ ውስጥ የግለሰቦችና የህዝቦች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩ ናቸው፡፡

## አንቀጽ 11
## የመንግስትና የሀይማኖት መለያየት

1. መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፡፡
2. መንግስታዊ ሃይማኖት አይኖርም፡፡
3. መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡ ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡

## አንቀጽ 12
## የመንግስት አሰራርና ተጠያቂነት

1. የክልሉ የመንግስት አሰራር ለህዝቡ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡



Scanned by CamScanner

2. ህዝቡ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ሊያነሳው ይችላል፣ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

3. ማንኛውም የስራ ኃላፊ ወይም የህዝቡ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጎድል ተጠያቂ ይሆናል።

# ምዕራፍ ሦስት

# መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች

## አንቀጽ 13

## ተፈፃሚነትና አተረጓጎም

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የክልሉ መንግስት የህግ አውጪ፣ የህግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካሎች በዚህ ምዕራፍ የተካተቱ ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው።

2. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግጋት፣ ከአለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ከሌሎች አለም አቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ።



Scanned by CamScanner

## ክፍል አንድ
## ሰብዓዊ መብቶች
## አንቀጽ 14
## የሕይወት፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት

ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በህይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት አለው።

## አንቀጽ 15
## በሕይወት የመኖር መብት

ማንኛውም ሰው በህይወት የመኖር መብት አለው።ማንኛውም ሰው በህግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ህይወቱን አያጣም።

## አንቀጽ 16
## የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው።

## አንቀጽ 17
## የነፃነት መብት

1. በህግ ከተደነገገው ስርዓት ውጭ ማንኛውም ሰው ነፃነቱን አያጣም።
2. ማንኛውም ሰው በህግ ከተደነገገው ስርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም።

## አንቀጽ 18
## ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከሉ

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት ኢ-ሰብአዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው።
2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ



Scanned by CamScanner

አይችልም። ለማንኛውም አላማና ሁኔታ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው።

3. ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛውም ስራ እንዲሰራ ማድረግ የተከለከለ ነው።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ‹‹በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ማሟላት›› የሚለው ሀረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም፡-

ሀ. ማንኛውም እስረኛ በእስር ባለበት ጊዜ በህግ መሰረት እንዲሰራ የተወሰነውን ወይም በገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ የሚሰራውን ማንኛውም ስራ፣

ለ. ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ህሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትኩ የሚሰጠው አገልግሎት፣

ሐ. የማህበረሰቡን ህይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማንኛውም አገልግሎት፣

መ. በሚመለከተው ህዝብ ፍቃድ በአካባቢው የሚፈጸምን ማንኛውንም የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት ስራ።

## አንቀጽ 19
## የተያዘ ሰው መብት

1. ማንኛውም ሰው ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ በሚያዝበት ጊዜ የቀረበበት ክስና የተያዘበት ምክንያት በሚገባው ቋንቋ ወዲያውኑ እንዲነገረው መብት አለው።
2. የተያዘ ሰው የተከሰሰበትን ጉዳይ በተመለከተ ያለመናገር መብት ያለው መሆኑ፣ ለመናገር ከመረጠ ደግሞ የሚሰጠው ቃል በፍርድ ቤት በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል መረዳት በሚችለው ቋንቋ እንደተያዘ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጠው መብት አለው።
3. ማንኛውም የተያዘ ሰው በተያዘ በአርባ ስምንት ሰዓት ውስጥ ፍርድ



Scanned by CamScanner

ቤት የመቅረብ መብት አለው፡፡ ይህም ጊዜ ሰውየው ከተያዘበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለማምጣት አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም፡፡ ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረበ በተጠረጠረበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽለት መብት አለው፡፡

4. የያዘው አካል ወይም የህግ አስከባሪ በጊዜው ገደቡ መሰረት ፍርድ ቤት በማቅረብ የተያዘበትን ምክንያት ካላስረዳ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነቱን እንዲያስከብርለት የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አለው፡፡ ሆኖም ፍትህ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በጥበቃ ስር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሊጠይቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ የሚወስነው ኃላፊ የሆኑት ህግ አስከባሪ ባለስልጣኖች ምርመራውን አጣርተው የተያዘው ሰው በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለውን መብት በሚያስከብር መልኩ መሆን አለበት፡፡

5. ማንኛውም ሰው በራሱ ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጥ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምን አይገደድም፡፡ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

6. የተያዘ ሰው በዋስ የመፈታት መብት አለው፡፡ ሆኖም በህግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤቱ ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፈታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 20
## የተከሰሰ ሰው መብት

1. የተከሰሰ ሰው ክስ ከቀረበበት በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለህዝቡ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አለው፡፡



Scanned by CamScanner

ሆኖም የተከራካሪዎችን የግል ህይወት፣ የህዝቡን የሞራል ሁኔታ ወይም የአገሪቱን ወይም የክልሉን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል።

2. የተከሰሰ ሰው ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገረውና ክሱን በጽሁፍ የማግኘት መብት አለው።

3. ማንኛውም ተከሳሽ በፍርድ ሂደት ጊዜ በተከሰሰበት ወንጀል እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት አለው። በምስክርነት እንዲቀርብም ያለመገደድ መብት አለው።

4. የተከሰሰ ሰው የቀረበበትን ማንኛውም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡበትን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችለውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቹ ቀርበው እንዲሰሙለት የመጠየቅ መብት አለው።

5. የተከሰሰ ሰው በመረጠው የህግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም ከሌለውና ፍትህ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ካጋጠመ ከመንግስት ጠበቃ የማግኘት መብት አለው።

6. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠበት ትእዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ተከሳሽ ቅሬታ ካለው ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል።

7. ተከሳሽ የፍርዱ ሂደት በማይገባው ቋንቋ በሚካሄድበት ጊዜ በመንግስት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጎምለት የመጠየቅ መብት አለው።

## አንቀጽ 21
## በጥበቃ ስር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰው መብት

1. በጥበቃ ስር ያለና በፍርድ የታሰረ ሰው ሰብአዊ ክብሩን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አለው።

2. ማንኛውም የታሰረ ሰው ከትዳር ጓደኛው፣ ከቅርብ ዘመዶቹ፣ ከጓደኞቹ፣ ከኃይማኖት አማካሪዎች፣ ከሐኪሞቹና ከህግ አማካሪዎቹ ጋር



Scanned by CamScanner

ወይም የመቀበል እና የኃይማኖቱን ወይም እምነቱን በግልም ሆነ ከሌሎች ጋር በይፋ የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ወይም የመግለጽ፣ መብትን ያካትታል።

2. በፌዴራል ህገ-መንግስት አንቀጽ 90(2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የኃይማኖት ተከታዮች ኃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸው የኃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ።

3. ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም።

4. ወላጆችና ሌሎች ህጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሰረት የኃይማኖታቸውንና የመልካም ስነ-ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው።

5. ኃይማኖትንና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው የህዝብን ደህንነት፣ሰላምን፣ትምህርትን፣ የህዝቡን የሞራል ሁኔታ፣ የሌሎች ዜጎችን መሰረታዊ መብቶች ነፃነቶችና መንግስት ከኃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ህጎች ይሆናል።

## አንቀጽ 28

## በሰብእና ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች

ኢትዮጵያ ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የአገሪቱ ህጎች በሰው ልጆች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች በተለይ የሰው ዘር የማጥፋት፣ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር ወይም ኢ-ሰብአዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈፀሙት ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም። በህግ አውጪው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግስት አካል ውሳኔዎች በምህረት ወይም በይቅርታ አይታለፍም።



Scanned by CamScanner

## ክፍል ሁለት

## ዴሞክራሲያዊ መብቶች

## አንቀጽ 29

## የአመለካከት ፣ ሃሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት

1. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሃሳቡን የመግለጽ ነፃነት አለው፡፡ ይህ ነፃነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሁፍ ወይም በህትመት በስነ-ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ ማንኛውንም አይነት መረጃና ሃሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል፡፡
3. የፕሬስንና የሌሎችን መገናኛ ብዙኃን እንዲሁም የስነ-ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል፡፡ የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል፡፡
   ሀ. የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን፣
   ለ. የህዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት እድልን፡፡
4. ለዴሞክራሲያዊ ስርአት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ሃሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሰራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡
5. በመንግስት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግስት ቁጥጥር ስር ያለ መገናኛ ብዙኃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችል ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል፡፡
6. እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሃሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው የአስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ



Scanned by CamScanner

ተመስርተው በሚወጡ ህጎች ብቻ ይሆናል። የወጣቶችን ደህንነት የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ህጋዊ ገደቦች በነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ። የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በህግ የሚከለከሉ ይሆናል።

## አንቀጽ 30
## የመሰብሰብ፣ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሳሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው። ከቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በህዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ፣ ሰላምን፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶችንና የህዝቡን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ስርአቶች ሊደነገጉ ይችላሉ።
2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት፣የሰውን ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብአዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ህጎች መሰረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም።

## አንቀጽ 31
## የመደራጀት መብት

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም አላማ በማህበር የመደራጀት መብት አለው። ሆኖም አግባብ ያለውን ህግ በመጣስ ወይም ህገ-መንግስታዊ ስርአቱን በህገ-ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ።



Scanned by CamScanner

## አንቀጽ 32
## የመዘዋወር ነፃነት

በፌደራል ህገ-መንግስት አንቀጽ 32 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ ወይም በህጋዊ መንገድ በክልሉ ውስጥ የሚገኝ ሰው በፈለገው የክልሉ አካባቢ የመዘዋወር፣የመኖር፣ ሐብት የማፍራትና የመያዝ እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከክልሉ የመውጣት ነፃነት አለው፡፡

## አንቀጽ 33
## በመንግስታዊና ህዝባዊ ስራዎች የመሳተፍ መብት

በክልሉ ውስጥ ነዋሪ የሆነና የክልሉን የስራ ቋንቋ የሚያውቅ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፌዴራሉና በዚህ ህገ-መንግስት መሰረት በማንኛውም የክልሉ መንግስታዊ ወይም ህዝባዊ ስራ ተቀጥሮ ወይም ተመርጦ የመስራት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 34
## የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች

1. በህግ ከተወሰነ የጋብቻ እድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣በብሔረሰብ ወይም በኃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው፡፡ በጋብቻ አፈፃፀም፣ በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው፡፡

   በፍቺም ጊዜ የልጆች መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ፡፡
2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፍቃድ ላይ ብቻ ይመሰረታል፡፡
3. ቤተሰብ ከህብረተሰብና ከመንግስት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው፡፡
4. በህግ በተለይ በሚዘረዘረው መሰረት በኃይማኖትና በባህል ስርአቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈፀሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ህግ ሊወጣ ይችላል፡፡



Scanned by CamScanner

5. ይህ ህገ-መንግስት የግልና የቤተሰብ ህግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፍቃድ በኃይማኖቶች ወይም በባህሎች ህጎች መሰረት መዳኘትን አይከለክልም፡፡ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 35
## የሴቶች መብት

1. ሴቶች ይህ ህገ-መንግስት በአረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡
2. ሴቶች በዚህ ህገ-መንግስት በተደነገገው መሰረት ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡
3. ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ቅርስ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ቅርስ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው፡፡ በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች አላማ በፖለቲካዊ፣በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግስት እና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡
4. ሴቶች ከጎጂ ባህል ተጽዕኖ የመላቀቅ መብታቸውን መንግስት ማስከበር አለበት፡፡ ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአእምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ህጎች፣ ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው፡፡
5. በመንግስት መስሪያ ቤቶች ወይም በግል ድርጅቶች ተቀጥረው የሚሰሩ ሴቶች፡-

   ሀ. የወሊድ ፍቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው፣ የወሊድ ፍቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሰራውን ስራ ሁኔታ፣የሴቷን ጤንነት የህፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በህግ ይወሰናል፡፡

   ለ. የወሊድ ፍቃድ በህግ በሚወሰነው መሰረት ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፍቃድን ሊጨምር ይችላል፡፡



Scanned by CamScanner

6. ሴቶች በክልሉ የልማት ፖሊሲዎች አቅድና በፕሮጀክት ዝግጅትና አፈፃፀም በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ሃሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

7. ሴቶች ንብረት የማፍራት፣የማስተዳደር፣የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው፡፡ በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ ማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡ እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው፡፡

8. ሴቶች የቅጥር፣የስራ እድገት፣የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው፡፡

9. ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣መረጃ እና አቅም የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 36
## የህፃናት መብት

1. ማንኛውም ህፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት

   ሀ. በህይወት የመኖር፣

   ለ. ስምና ዜግነት የማግኘት፣

   ሐ. ወላጆቹን ወይም በህግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣

   መ. ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርት በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት በሚያደርሱ ስራዎች እንዲሰሩ ያለመገደድ ወይም ከመስራት የመጠበቅ፣

   ሠ. በትምህርት ቤቶች ወይም በህፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ላይ ከሚፈጸም ወይም ከጭካኔና ኢ-ሰብዓዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን፡፡



Scanned by CamScanner

2. ህፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግስታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋማት፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለስልጣኖች ወይም በህግ አውጪ አካላት የህፃናት ደህንት በቀደምትነት መታሰብ አለበት።
3. ወጣት አጥፊዎች በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋም የሚገኙ በመንግስት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው።
4. ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ህፃናት በጋብቻ ውስጥ ከተወለዱ ህጻናት ጋር እኩል መብት አላቸው።
5. መንግስት ለአጓለ-ማውታን ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል። በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ስርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሰረቱ ያበረታታል።

## አንቀጽ 37
## ፍትህ የማግኘት መብት

1. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ውሳኔ ወይም ፍርድ፣
   ሀ. ማንኛውም ማህበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፣
   ለ. ማንኛውም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው።



Scanned by CamScanner

# አንቀጽ 38
## የመምረጥና የመመረጥ መብት

1. ማንኛውም የክልሉ ህዝብ በቀለም፣ በዘር፣በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት፡፡
   ሀ. በቀጥታ እና በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በህዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ፣
   ለ. እድሜው 18 አመት ሲሞላ በህግ መሰረት የመምረጥ፣
   ሐ. በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 33 የተፃፈው እንደተጠበቀ ሆኖ እድሜው 21 አመት ሲሞላው መመረጥ፣
   መ. ምርጫው ሁሉ አቀፍ፣በእኩልነት ላይ የተመሰረተና በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነፃነት የሚገልጽበት ዋስትና የሚሰጥ ሆኖ በሐገራችን ህገ-መንግስትና በምርጫ ህግ መሰረት መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም ሰው በፖለቲካ ድርጅቶች፣በሰራተኞች፣ በንግድ፣ በአሰሪዎችና በሙያ ማህበራት ለተሳትፎ ድርጅቱ የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ በፍላጎቱ አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከቱት ድርጅቶች ውስጥ በኃላፊነት ቦታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይፈጽማሉ፡፡
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ድንጋጌዎች የህዝብን ጥቅም ስፋ ባለ ሁኔታ የሚነኩ እስከሆነ ድረስ በህዝባዊ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡



Scanned by CamScanner

## አንቀጽ 39
## የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ መብቶች

የሐረሪ ህዝብ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብት በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው። በዚህ መሰረት የሐረሪ ህዝብ፤

1. የራሱን ብሔራዊ ማንነት የመጠበቅና የማስከበር፣ ቅርሱንና ታሪኩን የመንከባከብ፣ የማበልጸግ እንዲሁም በቋንቋው የመጠቀም፣ቋንቋውን የማሳደግና ባህሉን የመግለጽ መብት አለው።
2. በራሱ መልከአ-ምድራዊ ክልል ውስጥ የራሱን ጉዳይ በራሱ የማከናወን፣ ራሱን የማስተዳደር እንዲሁም በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት ውስጥ በነፃነትና አድልዎ በሌለበት፣ ተገቢና ፍትኃዊ በሆነ አግባብ ውጤታማ ተሳትፎ ለማድረግ መብት አለው።
3. ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት፣ በራሱ መልከአ-ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግስታዊ ተቋማት የማቋቋምና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብት አለው።
4. በዚህ አንቀጽ በተራ ቁጥር 1 ፣ 2 እና 3 የተጠቀሱት መብቶች ታገዱ፣ ተረገጡ፣ ወይም ተሸራረፉ ብሎ ባመነበትና እነኝህም መብቶች በኢፌዴሪ መንግስት አንድነት ጥላ ስር ሆኖ ሊያስተካክላቸው ባልቻለበት ጊዜ እስከ መገንጠል ድረስ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብቱን ተግባራዊ ያደርጋል፣
5. የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብት በስራ ላይ የሚውለው፣

   ሀ. የመገንጠሉ ጥያቄ በሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ፣

   ለ. የጉባኤው የመገንጠል ውሳኔ በደረሰው በሶስት አመት ጊዜ ውስጥ



Scanned by CamScanner

የፌዴራሉ መንግስት ህዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፣

ሐ. የመገንጠሉ ጥያቄ በህዝበ ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ፣

መ. የፌደራሉ መንግስት መገንጠሉን ለጠየቀው ለሐረሪ ህዝብ ስልጣኑን ሲያስረክብና፣

ሠ. በህግ በሚወሰነው መሰረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው።

6. በዚህ ህገ-መንግስት ውስጥ « የሐረሪ ህዝብ» ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው ሊግባቡ የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለን ብለው የሚያምኑና የስነ-ልቦና አንድነት ያላቸው በተያያዘ መልካአ-ምድር የሚኖሩ ህብረተሰብ ማለት ነው።

## አንቀጽ 40
## የንብረት መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ/መሆኗ ይከበርለታል/ ይከበርላታል። ይህ መብት የህዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በህግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረትን የመሸጥ፣የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል።
2. ለዚህ አንቀጽ አላማ « የግል ንብረት» ማለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም ህጋዊ ሰውነት በህግ የተሰጣቸው ማህበራት ወይም አግባብ በአላቸው ሁኔታዎች በህግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማህበረሰቦች በጉልበታቸው፣ በፈጠራ ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና ተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው።
3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግስትና የህዝብ ብቻ ነው። መሬት የማይሸጥ፣ የማይለወጥ



Scanned by CamScanner

የህዝቦች የጋራ ንብረት ነው፡፡

4. የክልሉ አርሶ አደሮች መሬት በነጻ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው፡፡ አፈፃፀሙን በተመለከተ ዝርዝር ህግ ይወጣል፡፡
5. የመሬት ባለቤትነት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ለግል ባለሀብቶች በህግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ያስከብርላቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡
6. ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ፣ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ መብት የመሸጥ፣የመለወጥ፣የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ በህግ ይወሰናል፡፡
7. የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 41
## የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶች

1. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ ወይም በክልሉ ውስጥ ለመኖር የሚፈልግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ስራ የመስራት መብት አለው፡፡
2. ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ መተዳደሪያውን፣ስራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው፡፡
3. የክልሉ ነዋሪዎች ሁሉ በመንግስት ገንዘብ በሚካሄዱ ማህበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው፡፡



Scanned by CamScanner

4. የክልሉ መንግስት የጤና፣የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ለህዝቡ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል፡፡

5. የክልሉ መንግስት የአካልና የአእምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ህፃናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የክልሉ ኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል፡፡

6. የክልሉ መንግስት ለስራ አጦችና ለችግረኞች ስራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፣ እንዲሁም በሚያካሄደው የስራ ዘርፍ ውስጥ የስራ እድል ለመፍጠር የስራ ፕሮግራሞችን ያወጣል፣ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል፡፡

7. የክልሉ መንግስት የክልሉ ነዋሪዎች ጠቃሚ ስራ የማግኘት እድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

8. መንግስት የባህልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ለስነ-ጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋጽኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

## አንቀጽ 42
## የሰራተኞች መብት

1. ሀ. የፋብሪካ፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትና የአገልግሎት ሰራተኞች፣ ገበሬዎች፣ የእርሻ ሰራተኞች፣ ሌሎች የገጠር ሰራተኞች ከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የስራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግስት ሰራተኞች የስራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማህበር የመደራጀት መብት አላቸው፡፡ይህ መብት የሰራተኛ ማህበራትና ሌሎች ማህበራትን የማደራጀት፣ ከአሰሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶችጋር የመደራደር መብትን ያካትታል፡፡

ለ. በንዑስ አንቀጽ (ሀ) የተመለከቱት የሰራተኛ ክፍሎች ስራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታቸውን የማሰማት መብት አላቸው፡፡



Scanned by CamScanner

ሐ. በንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) መሰረት እውቅና ባገኙ መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግስት ሰራተኞች በህግ ይወሰናሉ፡፡

መ. ሴቶች ሰራተኞች ለተመሳሳይ ስራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

2. ሰራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የስራ ሰአት እረፍት፣የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የእረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የህዝብ በአላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የስራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

3. እነዚህ መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ህጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት አይነት ሰራተኛ ማህበራት ስለሚቋቋምበት እና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ስርአት ይደነግጋሉ፡፡

## አንቀጽ 43
## የልማት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

2. ዜጎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትንም ማህበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሃሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

3. የልማት እንቅስቃሴ ዋና አላማ የክልሉን ነዋሪዎች እድገትና መሰረታዊ ፍላጎት ማሟላት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 44
## የአካባቢ ደህንነት መብት

1. የክልሉ ነዋሪዎች ንጹህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው፡፡



Scanned by CamScanner

2. የክልሉ መንግስት በሚያካሄዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግስት በቂ እርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## ምእራፍ አራት
## የክልሉ መንግስት አደረጃጀትና የስልጣን ክፍፍል
### አንቀጽ 45
### የክልሉ አስተዳደር እርከኖች

1. የሐረሪ ህዝብ ክልል መንግስት በክልል እና በቀበሌ የተዋቀረ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች የአስተዳደር መዋቅሮች ሊያዋቅርና ስልጣንና ተግባራቸውን ሊወስን ይችላል፡፡
2. ሐረር ከተማ የራሱ አስተዳደር ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡

### አንቀጽ 46
### የክልሉ መንግስት የስልጣን አካላት

1. የክልሉ ከፍተኛ የህግ አውጪ አካል የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለወከለው ህዝብ ነው፡፡
2. የክልሉ ከፍተኛ የህግ አስፈፃሚ አካል የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሲሆን ተጠሪነቱም ለክልሉ ምክር ቤት ነው፡፡
3. የክልሉ የዳኝነት ስልጣን የክልሉ ፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፡፡

### አንቀጽ 47
### የክልሉ መንግስት ስልጣንና ተግባር

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት ውስጥ በግልጽ ተለይተው ለፌዴራሉ መንግስት ወይም ለፌዴራሉ መንግስትና ለክልሉ መንግስት በጋራ ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ውጪ ያሉ ማናቸውም ስልጣንና ተግባር የክልሉ መንግስት ይሆናል፡፡



Scanned by CamScanner

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የሰፈረው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት :-

2.1 የክልሉን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ፖሊሲ ስትራቴጂና እቅድ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፡፡

2.2 የክልሉን ህገ-መንግስትና ሌሎች ህጎችን ያወጣል፣ ያስፈጽማል፡፡

2.3 የፌዴራል መንግስት በሚያወጣው ህግ መሰረት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል፡፡

2.4 ራስን በራስ ማስተዳደርን አላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያዋቅራል፡፡ የህግ የበላይነት የሰፈነበት ዲሞክራሲያዊ ስርአት ይገነባል፤ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስትና ይህንን ህገ-መንግስት ይጠብቃል፣ ይከላከላል፡፡

2.5 የክልሉን መስተዳድር ሰራተኞች አስተዳደርና የስራ ሁኔታዎችን በተመለከተ ህግ ያወጣል፣ያስፈጽማል፣ ይህን በሚያስፈጽምበት ጊዜ የሀገሪቱን የትምህርት፣ የስልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

2.6 የክልሉን የፖሊስ ሀይል ያደራጃል፣ይመራል፣ የክልሉን ሰላምና ፀጥታ ይጠብቃል፡፡

2.7 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 28 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆነው በህግ መሰረት ምህረት ወይም ይቅርታ ያደርጋል፡፡

2.8 ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ ግብርና ሌሎች ታክሶችን ይጥላል፡፡

2.9 በክልሉ መስተዳድርና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የስራ ግብር ይጥላል፡፡

2.10 የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናል፣ይሰበስባል፡፡



Scanned by CamScanner

2.11 የእርሻ ስራ ገቢ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡

2.12 በክልሉ በግል ባለቤትነት ስር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ይሰበስባል፣ በክልል መስተዳድሩ ባለቤትነት ስር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላል፡፡

2.13 በክልል መስተዳድር ባለቤትነት ከሚገኙ ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ፣ የስራ ግብር፣ የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ ይሰበስባል፡፡

2.14 ከፌዴራሉ መንግስት ጋር፤

ሀ. በጋራ ከሚያቋቁማቸው የልማት ድርጅቶች የሚገኘውን የንግድ ትርፍ ግብር፣የስራ ግብር፣የሽያጭና የኤክሳይዝ ታክስ በህጉ መሰረት ይካፈላል፡፡

ለ. ከድርጅቶች የንግድ ትርፍና ከባለ አክስዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብር እና የሽያጭ ታክስ በህጉ መሰረት ይካፈላል፡፡

ሐ. ከከፍተኛ የማእድን ስራዎችና ከማንኛውም የፔትሮሊየም የጋዝ ስራዎች የሚገኘውን የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በህጉ መሰረት ይካፈላል፡፡

2.15. በክልሉ መስተዳድር አካላት ከሚሰጡ ፍቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል፤ ይሰበስባል፡፡

2.16. ከደን የሚገኝ የሮያሊቲ ክፍያን ይወስናል፣ይሰበስባል፡፡

2.17. በክልሉ ውስጥ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያወጣል፡፡



Scanned by CamScanner

## ምእራፍ አምስት

## የክልሉ ምክር ቤት አወቃቀርና አወካከል፣ ስልጣንና ተግባር

### አንቀጽ 48

### የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት

የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት 36 አባላት ያሉትና በሁለት ጉባኤዎች የተዋቀረ የክልል ምክር ቤት ነው።

### አንቀጽ 49
### የምክር ቤቱ ጉባኤዎች

1. የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት ሁለት ጉባኤዎች አሉት፡-
   ሀ. የህዝብ ተወካዮች ጉባኤና

   ለ. የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ናቸው።
2. የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 50(1) እንደተመለከተው የሚወከሉ ሃያ ሁለት አባላት ይኖሩታል።
3. የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 50(2) እንደተመለከተው የሚወከሉ 14 የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት ይኖሩታል።

### አንቀጽ 50
### የጉባኤዎች አከፋፈል፣አወካከልና አመራረጥ

1. የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ አባላት በሁለት የምርጫ ክልሎች የሚወከሉ አባላት ያሉት ጉባኤ ነው። አወካከሉ ፡-
   ሀ. ከጁገል ምርጫ ክልል 4 አባላትና

   ለ. ከጁገል ውጭ ካሉት የከተማ ቀበሌዎችና የገጠር ቀበሌ ገበሬ ማህበራትን የሚያጠቃልል የምርጫ ክልል 18 አባላት ይመረጣል።
2. የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ አባላት በክልሉ ውስጥና ከክልሉ ውጭ በሌላ



Scanned by CamScanner

በኢትዮጵያ ክልሎችና ከተሞች ከሚኖሩ የሐረሪ ብሔረሰብ አባላት ይመረጣል።

3. የጉባኤው አባላት ምርጫ ነፃና ቀጥተኛ በሆነ ድምጽ በሚስጥር በመስጠት ስርአት ይፈፀማል።

## ክፍል አንድ
## ስለ ክልሉ ምክር ቤት
## አንቀጽ 51
## የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

1. የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት የህዝብ ተወካዮች ጉባኤና የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በጋራ የሚሰበሰቡበት ምክር ቤት ነው። በዚህ ህገ-መንግስት መሰረት የክልሉ ህግ አውጪና በክልሉ የውስጥ ጉዳዮች ላይ የበላይ የፖለቲካ ስልጣን ባለቤት ነው።
2. የሐረሪ ህዝብ ክልል ምክር ቤት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ. የክልሉን ህገ-መንግስትና ሌሎች ህጎችን ያወጣል።

ለ. በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 79 በተደነገገው መሰረት የክልሉን ህገ-መንግስት ያሻሽላል።

ሐ. የፌዴራል ህገ-መንግስት ለክልሎች የተሰጠውን ስልጣን በክልሉ ተግባራዊ ያደርጋል።

መ. ለክልሉ ፕሬዝዳንትነት በሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ጠቋሚነት የሚቀርበውን እጩ በ2/3ኛ ድምጽ መርምሮ ይመርጣል።

ሠ. የክልሉን የውስጥ አስተዳደር ያዋቅራል፣ ያደራጃል።

ረ. የክልሉን ህዝብ ደህንነትና ፀጥታን በሚመለከት ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ያወጣል፡

ሰ. በህዝብ ተወካዮች ጉባኤና በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚቀርቡለትን አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ፖሊሲዎችን



Scanned by CamScanner

መርምሮ ያፀድቃል፡፡

ሸ. በክልሉ ፕሬዝዳንት የቀረቡትን ምክትል ፕሬዝዳንት፣ የክልል አስፈፃሚ /ካብኔ/ አባል የሆኑ የቢሮ ኃላፊዎችና ሌሎች ተመሳሳይ ስልጣን ያላቸውን ኃላፊዎች ሹመት ያጸድቃል፡፡

ቀ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፣ ምክትል ፕሬዝዳንት፣ ዋና ኦዲተር እና የፖሊስ ኮሚሽነር ይሾማል፡፡

በ. በክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የሚቀርቡትን ዳኞች ሹመት ያጸድቃል፡፡

ተ. የክልሉን የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ፣ ደንብና መመሪያ ያወጣል፡፡

ቸ. ለክልሉ በተሰጠው የገቢ ምንጭ ወሰን ግብርና ታክስ ይጥላል፡፡

ነ. የክልሉን አመታዊ በጀት ያፀድቃል፡፡

ኘ. በክልሉ ውስጥ ማናቸውም ድንገተኛ የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፡፡

አ. የክልሉን መንግስት የገቢ ምንጮች የሚመለከቱ ህጎች ያወጣል፡፡

ወ. በህጉ መሰረት ምህረት ያደርጋል፣ የክልሉን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፡፡ የፀጥታና የፖሊስ ሃይሉን ያቋቁማል፡፡

የ. የክልሉ ርእሰ መስተዳድርና ሌሎች የክልሉን መንግስት ባለስልጣናትን ለጥያቄ ይጠራል፣ የአስፈፃሚውን አካል አሰራር ይመረምራል፡፡

## አንቀጽ 52
## የምክር ቤቱ አመራርና አሰራር

1. ምክር ቤቱ የራሱ አፈ- ጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤ ይኖሩታል፡፡



Scanned by CamScanner

2. እንደአስፈላጊነቱ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ይኖሩታል፡፡
3. አፈ- ጉባኤው በህዝብ ተወካዮች ጉባኤ በኩል እንዲሁም ምክትል አፈ-ጉባኤ በሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ በኩል ቀርበው በምክር ቤቱ በ2/3ኛ ድምጽ ይመረጣሉ፡፡

## አንቀጽ 53
## የአፈ- ጉባኤው ስልጣንና ተግባር

1. የምክር ቤቱን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራል፡፡
2. የምክር ቤቱን ጠቅላላ ስራዎች ያስተዳድራል፡፡
3. በምክር ቤቱ አባላት ላይ የሚወሰኑ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ያስፈጽማል፡፡
4. የአፈ- ጉባኤው ሌሎች ስራዎች በዝርዝር የሚወጣ ሌላ ህግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 54
## የምክትል አፈ- ጉባኤው ስልጣንና ተግባር

1. በአፈ- ጉባኤ ተለይቶ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡
2. አፈ- ጉባኤው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡

## አንቀጽ 55
## የምክር ቤቱ አባላት መብትና ግዴታ

1. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል በምክር ቤቱ በሚሰጠው ድምጽ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም፤ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም፡፡
2. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ምክር ቤቱ ፍቃድ አይያዝም፤ በወንጀልም አይከሰስም፡፡
3. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል የመረጠው ህዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ ከምክር ቤት አባልነት ይወገዳል፡፡ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡



Scanned by CamScanner

## አንቀጽ 56
## የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜና የስራ ዘመን

1. ምክር ቤቱ በአመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል።
2. የምክር ቤቱ አባላት የስራ ዘመን ለአምስት አመት ነው። የስራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሄዶ ይጠናቀቃል። የቀድሞው ምክር ቤት የስራ ዘመን በተጠናቀቀ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ስራውን ይጀምራል።
3. የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማይኖርበት ወቅት አፈ-ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል። የክልሉ ርእሰ መስተዳድር ወይም ከምክር ቤት አባላት መካከል ከ1/3ኛ በላይ የሚሆኑት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ-ጉባኤው ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት።
4. የምክር ቤቱ ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል። ሆኖም ስብሰባው በዝግ እንዲካሄድ በአባላቱ ወይም በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ከተጠየቀና ከምክር ቤት አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ጥያቄውን ከደገፉት ዝግ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል።

## አንቀጽ 57
## የውሳኔ አሰጣጥና የአሰራር ስነ-ስርዓቶች

1. ከሁለቱ ጉባኤዎች ከያንዳንዳቸው ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
2. ማንኛውም ውሳኔ የሚተላለፈው በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በተገኙት አባላት አብላጫ ድምጽ ይሆናል።
3. ምክር ቤቱ አሰራሩንና የሕግ አወጣጥ ሂደቱን አስመልክቶ ዝርዝር ህጎችን ሊያወጣ ይችላል።



Scanned by CamScanner

# ክፍል ሁለት
# የጉባኤዎች ስልጣንና ተግባር
## አንቀጽ 58
## የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

የህዝብ ተወካዮች ጉባኤ በክልሉ ምክር ቤት ከሚኖረው ስልጣንና ተግባር በተጨማሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

1. ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማትና የማህበራዊ ልማት ፖሊሲ ስትራቴጂን በተመለከተ ረቂቅ ህግ ያመነጫል፣ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል::
2. የግብር እና ታክስ አዋጆችን ያመነጫል፣ ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስፀድቃል::
3. የክልሉን በጀት ገምግሞ ለክልሉ ምክር ቤት ያቀርባል::
4. ከክልሉ የምክር ቤት አባላት መካከል ለአፈ-ጉባኤነት አንድ አባል ይጠቁማል::
5. የጉባኤውን ስብሰባ የሚመሩ አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈ- ጉባኤና
6. ቃለ-ጉባኤ የሚይዝ አንድ ፀሐፊ ይመርጣል::

## አንቀጽ 59
## የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር

1. የሐረሪ ብሔረሰብ ቋንቋና ባህልን በሚመለከት ፖሊሲና ህግ ያወጣል::
2. በክልሉ ውስጥ የሐረሪ ብሔረሰብ ታሪክና ባህል የሚያንጸባርቁ ቅርፃቅርጾች፣ የመቃብር ቦታዎች፣ የመስኪድና የአድባራት አጠባበቅን በሚመለከት መመሪያ ያወጣል::
3. የሐረሪ ብሔረሰብ በፌዴራል መንግስት በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚወክሉ ወይም የሚወክል አባላትን ወይም አባልን ይመርጣል::
4. የክልሉን ፕሬዝዳንትና የምክር ቤቱን ምክትል አፈ-ጉባኤ ይጠቁማል::
5. የጉባኤውን ስብሰባ የሚመሩ አፈ-ጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤና



Scanned by CamScanner

6. የጉባኤውን ቃለ-ጉባኤ የሚይዝ አንድ ፀሐፊ ይመርጣል፡፡
7. የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 39 መሰረት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## ምስራፍ ስድስት
## የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት
## አንቀጽ 60
## ስለ አስፈፃሚነት ስልጣን

1. የክልላዊ መንግስቱ ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ስልጣን የተሰጠው ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እና ለክልሉ ፕሬዝዳንት ነው፡፡
2. የመስተዳድሩ ምክር ቤት አባላት በመንግስት ተግባራቸው በጋራ ለሚሰጡት ውሳኔ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 61
## የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ፕሬዝዳንቱ፣ምክትል ፕሬዝዳንቱ፣ የቢሮ ኃላፊዎችና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወስናቸው ሌሎች አባላት የሚገኙበት አካል ነው፡፡
2. ፕሬዝዳንቱና የክልሉ አስፈፃሚ አካላት በዚህ ህገ-መንግስትና በሌሎች ህጎች የሚሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡
3. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ሰብሳቢ ፕሬዝዳንቱ ይሆናሉ፡፡
4. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት እና ለክልሉ ፕሬዝዳንት ይሆናል፡፡



Scanned by CamScanner

## አንቀጽ 62
## የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ስልጣንና ተግባር

በፌዴራል ህገ-መንግስት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል ፡-

1. በፌዴራል መንግስት፣ በክልሉ ምክር ቤት እና በሐረሪ ጉባኤ የወጡት ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡-
2. የክልሉን የመስተዳድር አካላትና ስራን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣተራል።
3. የክልሉን ማህበራዊ እድገትና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን የሚያስችሉ እቅዶችና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ሲፀድቅም ተግባራዊ ደርጋል።
4. የክልሉን መስተዳድር አመታዊ በጀት በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል።
5. የክልሉን ቢሮዎችና አስፈፃሚ አካላት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል።
6. ህግና ስርዓት በክልሉ መከበሩን ያረጋግጣል።
7. የልማት፣የማህበራዊ ጉዳይ፣ ጸጥታና ደህንነትን በሚመለከት የህግና የፖሊሲ ረቂቆችን ለክልሉ ም/ቤት ያቀርባል፣ሲጸድቅም በስራ ላይ ያውላል።
8. በክልሉ ምክር ቤት በሚሰጠው ስልጣን መሰረት ደንቦችና መመሪያዎችን ያወጣል።
9. ስለ ስራው እንቅስቃሴ ለክልሉ ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል።
10. በምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
11. በዚህ ህገ-መንግስት መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል።



Scanned by CamScanner

12. በክልሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን አስፈላጊ የሆኑ ተቋማትን በህግ ሊያዋቅር ይችላል።

## አንቀጽ 63
## የፕሬዝዳንቱ አሰያየም

1. ፕሬዝዳንቱ በሀረሪ ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት የሚመረጥ ይሆናል።
2. የፕሬዝዳንቱ የስራ ዘመን የክልሉ ምክር ቤት የስራ ዘመን ይሆናል።
3. ፕሬዝዳንቱ በምክር ቤቱ ፊት ቃለ-መሀላ መፈጸም ይኖርበታል። የቃለመሀላው ይዘት እንደሚከተለው ይሆናል።

   "እኔ ______________ በዛሬው እለት የሐረሪ ህዝብ ክልል ፕሬዝዳንት በመሆን ስራዬን ስጀምር የተጣለብኝን ከፍተኛ ሃላፊነት በታማኝነት ለመፈጸም ቃል እገባለሁኝ።"

## አንቀጽ 64
## የፕሬዝዳንቱ ስልጣንና ተግባር

1. ፕሬዝዳንቱ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

   ሀ. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤቱን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይወክላል።

   ለ. የክልሉ ምክር ቤት የሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ እና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚያወጡአቸውን ህጎች፣ ደንቦች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈጻሚነት ይከታተላል፣ ያስፈጽማል።

   ሐ. የክልሉን ምክትል ፕሬዝዳንት፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንቱን፣ ዋና ኦዲተር፣ምክትል ዋና ኦዲተር እና የፖሊስ ኮሚሽነር፣ የክልሉን መስተዳድር ምክር ቤት



Scanned by CamScanner

አባላትና ሌሎች የክልሉ መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎችን ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያሾማል።

መ. በንኡስ አንቀጽ (ሐ) ስር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ምክር ቤት ሊሰበሰብ ባልቻለበት ጊዜ ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን ኃላፊዎች በጊዜያዊነት መድቦ ያሰራል።

ሠ. ከክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት ውጪ የሆኑ ኃላፊዎች ምክትል ቢሮ ኃላፊዎች ኮሚሽነሮችና ሌሎች የስራ ኃላፊዎችን ይሾማል።

ረ. የካቢኔ አባላት፣ የቢሮ ኃላፊዎች ወይም የጽህፈት ቤት ኃላፊዎች ችግር ሲኖርባቸው በማገድና ለክልሉ ምክር ቤት በማቅረብ ያስወግዳል።

ሰ. የብሔራዊ ክልሉን ደህንነት ለማስጠበቅና ህግና ስርዓትን ለማስከበር የተቋቋሙትን ክልል አቀፍ የፀጥታና የፖሊስ ሀይሎች በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል።

ሸ. በክልሉ የሚገኙትን የበታች የአስተዳደር እርከኖችን ስራ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል።

## አንቀጽ 65

## የሐረሪ ህዝብ ክልል ፕሬዝዳንት ጽህፈት ቤት

ፕሬዝዳንቱ በዚህ ህገ-መንግስትና በሌሎች ህጎች የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ይቻለው ዘንድ የራሱ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 66

## የምክትል ፕሬዝዳንቱ ስልጣንና ተግባር

1. ምክትል ፕሬዝዳንቱ ተጠሪነቱ ለፕሬዝዳንቱ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡-



Scanned by CamScanner

ሀ. በክልሉ ፕሬዝዳንትና በክልል መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰጡትን ተግባራትን ያከናውናል፡፡

ለ. ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ወይም ስራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት
## ስለ ፍርድ ቤቶች አወቃቀርና የዳኝነት ስልጣን
### አንቀጽ 67
### ስለ ነፃ የዳኝነት አካል መቋቋም

1. በክልሉ ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ህገ-መንግስት ተቋቁሟል፡፡
2. የዳኝነት ስልጣንን ከመደበኛ ፍርድ ቤት ወይም በህግ የመዳኘት ስልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጪ የሚያደርግና በህግ የተደነገገውን የዳኝነት ስርአት የማይከተል ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም፡፡

### አንቀጽ 68
### ስለ ባህላዊና ኃይማኖታዊ ዳኝነት

1. የሀይማኖትና የባህል ፍርድ ቤቶች በሚወጣ ዝርዝር ህግ መሰረት ሊቋቋሙ ወይም እውቅና ሊሰጣቸው ይችላል፡፡
2. ይህ ህገ መንግስት ከመጽደቁ በፊት በመንግስት እውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ ሀይማኖታዊና ባህላዊ የዳኝነት አካላት በዚህ ህገ መንግስት እውቅና አግኝተው ይደራጃሉ፡፡

### አንቀጽ 69
### የዳኝነት ስልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፡፡
2. በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማናቸውም የመንግስት አካል ባለስልጣን ወይም ሌላ ተጽእኖ ነፃ ነው፡፡



Scanned by CamScanner

3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ ከህግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም።

4. ማንኛውም ዳኛ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በህግ የተወሰነው የጡረታ እድሜ ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከዳኝነት ስራው አይነሳም።

   ሀ. የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዳኞች የዲሲፒሊን ህግ መሰረት ጥፋት ፈጽሟል ወይም ጉልህ የሆነ የስራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወስን ወይም፣

   ለ. በህመም ምክንያት ዳኛው ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስንና፣

   ሐ. የጉባኤው ውሳኔ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ በአባላቱ አብላጫ ድምጽ ተደግፎ ሲጸድቅ።

5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት አንድን ዳኛ ከዳኝነት ስራው የሚያስነሳው ጥፋት ፈጽሟል ብሎ ጉባኤው ካመነበት ጉዳዩ በክልሉ ምክር ቤት እስኪወሰን ድረስ ከዳኝነት ስራው ይታገዳል።

6. የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም።

## አንቀጽ 70

## የፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና ስልጣን

1. የክልሉ የዳኝነት አካል በጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ በከፍተኛ ፍርድ ቤትና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይደራጃል።

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

   ሀ. ክልላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ከፍተኛውና የመጨረሻው የዳኝነት ስልጣን፣

   ለ. በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የፌዴራል መንግስት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣንና፣



Scanned by CamScanner

ሐ. ማንኛውም ክልላዊ ፍርድ ቤት የሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሲኖርበት በሰበር የማየት ስልጣን ይኖረዋል፡፡ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡

3. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከክልላዊ ስልጣኑ በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡፡
4. የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ መሰረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል፡፡
5. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባለው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣኑ መሰረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል፡፡
6. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት አካላቱን የሚያስተዳድርበትን በጀት ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፣ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል፡፡
7. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት በውክልና ለሚሰሩት ፌዴራላዊ የዳኝነት ተግባር ከፌዴራል መንግስት የበጀት ማካካሻ ይሰጣቸዋል፡፡

## አንቀጽ 71
## የዳኞች አሿሿም

1. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት በክልሉ ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡
3. የክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ሹመት ለክልሉ ምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት



Scanned by CamScanner

የፌዴራሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በእጩዎቹ ላይ ያለውን አስተያየት ከራሱ መግለጫ ጋር ለክልሉ ም/ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት። ሆኖም የፌዴራል ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ የተጠየቀውን አስተያየት በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የክልሉ ምክር ቤት የእጩ ዳኞች ሹመት ያጸድቃል።

## አንቀጽ 72

## ስለ ክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ መቋቋም

1. በክልሉ ውስጥ ዳኞች በአብላጫ ድምጽ የሚወከሉበት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ይቋቋማል።
2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት የጉባኤው ሰብሳቢ ይሆናል።
3. የጉባኤው አባላት ዝርዝር እንዲሁም ስልጣንና ተግባር በህግ ይወሰናል።

## አንቀጽ 73
## ህገ-መንግስቱን ስለመተርጎም

1. የህገ-መንግስታዊ ክርክር ጉዳይ ሲነሳ በህገ-መንግስት ተርጓሚ ኮሚስዮን ውሳኔ ያገኛል።
2. የህገ-መንግስት ተርጎሚ ኮሚስዩን የህገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሚያቀርብለት ህገ-መንግስታዊ ጉዳይ ላይ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።
3. የህገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሲዮን የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።
   ሀ. በኢፌዴሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሐረሪ ተወካይ ሰብሳቢ
   ለ. በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከሐረሪ ክልል ተወካዮች መካከል አንደኛው ምክትል ሰብሳቢ ሁለተኛው ፀሐፊ ሆነው በኮሚሲዮኑ ይመረጣሉ።



Scanned by CamScanner

ሐ. በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤና ከህዝብ ተወካች ጉባኤ ከእያንዳንዱ ጉባኤ የሚወከሉ ሁለት ሁለት ተወካዮች አባላት ፡፡

መ. በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የቀድሞ ፕሬዝዳንት/ ፕሬዝዳንቶች/ ድምጽ ሳይሰጡ የሚሳተፉበት፡፡

## አንቀጽ 74
## የህገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ

1. የክልሉ ህገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በዚህ ህገ መንግስት ተቋቁሟል፡፡
2. የክልሉ ህገ- መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አስራ አንድ አባላት ይኖሩታል፡፡
3. አባላቱም የሚከተሉት ናቸው ፡-

   ሀ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ----------- ሰብሳቢ፣

   ለ. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዝዳንት------------ ምክትል ሰብሳቢ፣

   ሐ. በክልሉ መስተዳድር ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በክልሉ ምክርቤት የሚሾሙ በሙያ ብቃታቸውና በስነ-ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የህግ ባለሙያዎች፣

   መ. በአፈ- ጉባኤው አቅራቢነት ከክልሉ ምክር ቤት አባላት መካከል የሚሰየሙ 3 ተወካዮች፣
4. የህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር፡-

   ሀ. የህገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ህገ መንግስታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ስልጣል ይኖረዋል ፡፡ በሚያደርገው ማጣራት መሰረት ህገ መንግስቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለህገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሲዮን በጉዳይ ላይ የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል ፡፡



Scanned by CamScanner

ለ. በክልሉ ህግ አውጪ አካል የሚወጡ ህጎች ከዚህ ህገ መንግስት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ ሲነሳና ጉዳዩም በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለ ጉዳይ ሲቀርብለት መርምሮ ለመጨረሻ ውሳኔ ለህገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ያቀርባል ።

ሐ. በፍርድ ቤቶች የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ ፦

1. ህገ መንግስቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይመልሳል በአጣሪው ጉባኤ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለጉዳይ ቅሬታውን ለህገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሲዮን በይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

2. የትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን ህግ መንግስታዊ ትርጉም ለህገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል ።

መ. የሚመራበትን ሥነ ሥርዓት አርቅቆ ለህገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።

## ምዕራፍ ስምንት

## አንቀጽ 75
## ስለ ቀበሌ አስተዳደር መቋቋም

1. የቀበሌ አስተዳደር የክልሉ የመጨረሻው መንግስታዊ የአስተዳደር እርከን ነው።
2. የቀበሌ አስተዳደር የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል፦
   ሀ. የቀበሌ ምክር ቤት፣
   ለ. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት፣
   ሐ. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ናቸው።
3. የቀበሌ መስተዳድር አካላት አደረጃጀትና ስልጣንና ኃላፊነታቸውን በተመለከተ በዝርዝር ህግ ይወጣል።



Scanned by CamScanner

ለ. በክልሉ ህግ አውጪ አካል የሚወጡ ህጎች ከዚህ ህገ መንግስት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ ሲነሳና ጉዳዩም በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለ ጉዳይ ሲቀርብለት መርምሮ ለመጨረሻ ውሳኔ ለህገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ያቀርባል ፡፡

ሐ. በፍርድ ቤቶች የህገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ ፡-

1. ህገ መንግስቱን መተርጓም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይመልሳል በአጣሪው ጉባኤ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለጉዳይ ቅሬታውን ለህገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሲዮን በይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን ህግ መንግስታዊ ትርጉም ለህገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል ፡፡

መ. የሚመራበትን ሥነ ሥርዓት አርቅቆ ለህገ መንግስት ተርጓሚ ኮሚሲዮን ያቀርባል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

## አንቀጽ 75
## ስለ ቀበሌ አስተዳደር መቋቋም

1. የቀበሌ አስተዳደር የክልሉ የመጨረሻው መንግስታዊ የአስተዳደር እርከን ነው፡፡
2. የቀበሌ አስተዳደር የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል፡-
   ሀ. የቀበሌ ምክር ቤት፣
   ለ. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት፣
   ሐ. የማህበራዊ ፍርድ ቤት ናቸው፡፡
3. የቀበሌ መስተዳድር አካላት አደረጃጀትና ስልጣንና ኃላፊነታቸውን በተመለከተ በዝርዝር ህግ ይወጣል፡፡



Scanned by CamScanner

# ምዕራፍ ዘጠኝ
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
## አንቀጽ 76
## የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ

1. ማንኛውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የህዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት እና ምክር ቤት በማይሰበሰብበት ጊዜ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 62 ንዑስ ቁጥር 11 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ ያወጣል።
2. የመስተዳድር ምክር ቤቱ የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌውን አውጥቶ በስራ ላይ ባዋለ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ አፈ-ጉባኤው ምክር ቤቱን አስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ ማስጸደቅ አለበት።
3. የመስተዳድር ምክር ቤት ያወጣው የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ በምክር ቤቱ ተቀባይነት ካገኘ ሊቆይ የሚችለው ለስድስት ወራት ብቻ ይሆናል። ሆኖም የክልሉ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲወሰን የአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌው በየአራት ወሩ ሊታደስ ይችላል።
4. የመስተዳድሩ ምክር ቤት እና ምክር ቤቱ በአስቸኳይ ጊዜ ድንጋጌ የሚያወጣቸው ድንጋጌዎችና የሚወስዳቸው እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 14፣16፣18 (1) እና 2፣21(1)፣ 24(1)፣ 25፣27(1) እና 39 የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ መሆን የለባቸውም።
5. በክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚታወጅበት ወቅት የክልሉ ምክር ቤት ከአባላቱና ከህግ ባለሙያዎች መርጦ የሚመድባቸው ሰባት አባላት ያሉት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃጸም መርማሪ ቦርድ ያቋቁማል። ቦርዱ በፌዴራሉ ህገ- መንግስት አንቀጽ 93 (6) የተጠቀሱት ስልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።



Scanned by CamScanner

## አንቀጽ 77
## የክልሉ ፖሊሲ አላማዎች

ማንኛውም የመንግስት አካል የፌደራሉንና የክልሉን ህገ-መንግስት፣ ሌሎች ህጎችና ፖሊሲዎች በስራ ላይ ሲያውል በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ-መንግስት ምእራፍ 10 ከአንቀጽ 85 እስከ 92 የተመለከቱትን ብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎችና አላማዎች መሰረት በማድረግ ነው።

## አንቀጽ 78
## የክልሉ ዋና ኦዲተር

1. የክልሉ ዋና ኦዲተር በመስተዳድሩ ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማል።
2. የክልሉ ዋና ኦዲተር የክልሉን ቢሮዎችና የሌሎች መስሪያ ቤቶች ሂሳቦችን በመቆጣጠር በክልሉ መንግስት የተመደበው ዓመታዊ በጀት በበጀት ዓመቱ እንዲሰሩ ለተወሰኑ ስራዎች በሚገባ መዋሉን ለክልል ምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።
3. የክልሉ ዋና ኦዲተር የመስሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለክልሉ ምክር ቤት አቅርቦ ያጸድቃል።

## አንቀጽ 79

## የህገ-መንግስት ማሻሻያ ሃሳብን ስለማመንጨትና ስለማሻሻል

1. የዚህ ህገ-መንግስት ምእራፍ 3 ድንጋጌዎች በፌደራል ህገ መንግስት አንቀጽ 105 ከተደረገው ውጪ ሊሻሻሉ አይችሉም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉት የህገ-መንግስቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት፦
   ሀ. የህገ-መንግስቱ የማሻሻያ ሃሳብ ከሁለቱ ጉባኤዎች ቢያንስ በአንዱ ሲነሳ፣



Scanned by CamScanner

ለ. የማሻሻያ ሃሳቡ በሁለቱም ጉባኤዎች ለየብቻቸው ውይይት ተደርጎበት ከእያንዳንዱ ጉባኤ በ2/3ኛ ድምጽ ሲደገፍ እና

ሐ. የክልሉ ምክር ቤት ማሻሻያውን በ2/3ኛ ድምጽ ሲያጸድቅ ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ 80
## ህገ- መንግስቱ የሚታተምባቸው ቋንቋዎች

ይህ ህገ-መንግስት በሐረሪኛ፣በኦሮምኛና በአማረኛ ቋንቋዎች ይታተማል፡፡ በሐረሪ እና በኦሮምኛ ቋንቋዎች መካከል የትርጉም ልዩነት ሲኖር የአማረኛ ቅጂ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡



Scanned by CamScanner